Ethiopian Academy of Sciences
የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ



የ10ኛ ዓመት የእረፍት መታሰቢያ የሥዕል ትርዒት
ከመጋቢት 30 እስከ ሚያዝያ 08 / 2014 ዓ.ም

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት

# አፈወርቅ ተክሌ

Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 1 4/14/2022 12:18:09 PM

# የአዘጋጁ መልእክት

የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሥነ ጥበባት ማዕከል በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ውስጥ ካሉ ዓበይት ክፍሎች መካከል አንዱ ሲሆን፤ መጋቢት 18፣ 2009 ዓ.ም በይፋ ሥራውን የጀመረ ማዕከል ነው። የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ከመንግሥት የተረከበውን እና በአዲስ አበባ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘውን በኢትዮጵያ ታሪክ በሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ስመጥር ጸሐፊ እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትን የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ መኖሪያ ቤትና ታሪካዊ ግቢ በዋና ጽሕፈት ቤትነት የቀድሞው ይዞታውን ሳይለቅ፣ ውበቱ እና ለአገልግሎት ምቹነቱ እንደተጠበቀ እየተገለገለበት ይገኛል። ይህ ቤት የታሪካዊ ቅርሱ አካል የሆኑ ጥንታዊ ኪነ ሕንፃ፣ ጥንታዊ የወፍ ቤት እና የአንበሳ ቤት አሉት።

የሥነ ጥበብ ማዕከሉ በዚሁ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጥንታዊ ቤት ውስጥ እያደራጀው ባለው አነስተኛ ሙዚየሙ እርሳቸውን የሚዘክሩ ልዩ ልዩ ስብስቦችን ይዟል። በሌላም በኩል በተለያየ ወቅት የተሰባሰቡ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን እና ፎቶግራፎችን የሚያሳይበት የቋሚ ዐውደ ርዕይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪም ማዕከሉ የሥነ ጥበብ ባለሞያዎች ፈጠራቸውን የሚያቀርቡበትና ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን የሚያጋሩበት ቋሚ መድረክ ያለው ሲሆን በእነዚህ ሥነጥበባዊ እንቅስቃሴዎች ጀማሪና አንጋፋ ሙያተኞች ሥራዎቻቸውን የሚያቀርቡባቸውን፣ ልምድ የሚለዋወጡባቸውን እና በአጫጭር ስልጠናዎች የሚሳተፉባቸውን መርሐ ግብሮች ያከናውናል። ከዚህም ባሻገር ማዕከሉ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ልዩ ልዩ ሥነ ጥበባትን እና ባህልን የተመለከቱ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን፣ ስልታዊ ቅንጅቶችን፣ ሀገር አቀፋዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችን ያደርጋል።

ማዕከላችን በተለይ በሥዕልና ቅርጻ-ቅርጽ ዘርፍ ለከያንያኑ በ"አርትስ ሪዚደንስ" ፕሮግራሙ አማካይነት በማዕከሉ ውስጥ የግል የመሥሪያ ስፍራ እና መጠነኛ በጀት መድቦላቸው ሥራቸውን ለሕዝብ እንዲያቀርቡ ሲደግፍ ቆይቷል። የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ የሥነ ጥበባት ማዕከል ከመጋቢት 30 - ሚያዚያ 8፣ 2014 ዓ.ም የታዋቂውን ሠዓሊ የእጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን 10ኛ ዓመት የዕረፍት መታሰቢያ በማስመልከት ይህን የሥዕል ትርዒት ሲያዘጋጅ ታላቅ ክብር ይሰማዋል። በዚህ ትርዒት ላይ 22 ያህል የሠዓሊው ኦሪጂናል ሥራዎች እንዲሁም ይገለገሉባቸው የነበሩ ብሩሾች፣ የቀለም መበጥበጫ እና ጅምር ቀለሞችን የያዘ ስብስብ ለዕይታ ቀርበዋል፡

የዚህ ትርዒት ዓብይ ዓላማ የታዋቂውን ሠዓሊ 10ኛ ዓመት የዕረፍት መታሰቢያ ማስታወስ ይሁን እንጂ የሠዓሊውን ቤት ጨምሮ በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኙ የሎሬት አፈወርቅ የሥዕል ሥራዎች በቋሚነት ለሕዝብ ዕይታ የሚቀርቡበት ሂደት እንዲፋጠን ማስታወስ፣ የሥዕል ዘርፉን ማነቃቃት እና የሙያ ልምድ ልውውጥን የሚከናወንነበትን ዓውድ መፍጠር ንዑሳን ዓላማዎቹ ናቸው። ለዚህም እንዲረዳ ከሥዕል ትርዒቱ በተጨማሪ የሠዓሊ አፈወርቅ ሙያዊና ሰዋዊ ማንነት ላይ የውይይት መድረክ እንዲከናወን ተደርጓል።

ማዕከላችን ለወደፊቱም የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ሥነ ጥበብ ላይ ያተኮሩ መድረኮችን እንደሚያከናውን ቃል እየገባን የዘርፉ ባለሙያዎችና ተቋማት አብረውት እንዲሠሩ በማክበር እንጠይቃለን። በመጨረሻም ይህ ዝግጅት የተሳካ እንዲሆን ድጋፍ ላደረጉልን ለኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአለ ሥነ ጥበብ እና ዲዛይን ት/ቤት፣ ለተዋነይ ስቱዲዮ፣ ለሮሚና ሬስቶራንት እና ጉልበትና ዕውቀታቸውን ለለገሱን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን።

**ይታገሱ ጌትነት**
የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ
ሥነ ጥበባት ማዕከል ዳይሬክተር



Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 2 4/14/2022 12:18:10 PM

# የኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ በአዋጅ ቁጥር 783/2005 የተቋቋመ መንግሥታዊ ያልሆነና ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። አካዳሚው ሳይንስን በማሳደግ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ልማትና ብልፅግና እንዲመጣና የተሻለ አገልግሎት እንዲኖር ፍላጎት ባላቸው ታዋቂ ምሁራን በ2005 ዓ.ም የተመሠረተ ተቋም ነው። በአሁኑ ወቅት 250 አባላት ያሉት ሲሆን፣ እነዚህኑ አባላቱን እንደየሙያቸው በስድስት ዘርፎች ማለትም በሳይንስ፣ በጤና፣ በእርሻ፣ በምሕንድስናና ቴክኖሎጂ፣ በማኅበረሰብ ሳይንስና ሥነሰብዓት እንዲሁም በሥነ ጥበባት ዘርፎች አዋቅሮ ሥራውን ይፈጽማል።

አካዳሚው የሳይንስ ሙዚየሞችና ኤግዚቢቶች ያሉት የሳይንስ ማዕከል፣ የአካዳሚ ፕሬስ፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ የሥነ ጥበባት ማዕከል እንዲሁም ለሳይንስ ትምህርት የሚያገለግሉ አገር በቀል ዛፎችንና መድሃኒትነት ያላቸው ዕፅዋትን የያዘ ሰፊ ግቢ አለው።

አካዳሚው በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን የመስጠት፣ በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረኮችን የማዘጋጀት፣ በኢትዮጵያ ሳይንስን ባህል ለማድረግ እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትና ዕውቀት ጥራቱን ጠብቆ እንዲስፋፋ የሚያግዙ መርሐ ግብሮችን ያከናውናል።

አካዳሚያችን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ከሰጣቸው የመንግሥት አካላት መካከል፣ የትምህርት ሚኒስቴር የቀድሞው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የቀድሞው የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን፣ የፕላንና የኢኮኖሚ ልማት ኮሚሽን፣ የፖሊሲ ጥናት ኢንሲቲቲዩት እና የባዮ-ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ይገኙበታል። የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የአፍሪካ አካዳሚዎች ኅብረት እና የዓለም አቀፍ የአካዳሚዎች ኅብረት አባል በመሆን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጋራ ሥራዎችን ይፈጽማል።


ከማዕከሎቹ አንዱ የሆነው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሥነ ጥበባት ማዕከል ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሥነ ጥበባዊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። የዚሁ አካል የሆነው የእጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የሥዕል ትርዒት ከብሔራዊ ሙዚየም የተገኙ ኦርጅናል ሥራዎች ስብስብ ለአንድ ሳምንት ለሕዝብ ዕይታ አብቅቷል። ይህ የሥዕል ትርዒት እንዲሳካ ያገዙትን ሁሉ እያመሰገንሁ፣ በአካዳሚያችን የሚካሄዱትን ባህል የማሳደግ ሥራዎች የሁላችንም በመሆናችው ወደ ማዕከላችን እየመጣችሁ እንድትጎበኙን እንዲሁም ገንቢ አስተያየታችሁን እንድትሰጡን በአክብሮት እጠይቃለሁ።

**ተከተል ዮሐንስ (ፕሮፌሰር)**
የኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ
ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር





Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 3 4/14/2022 12:18:13 PM



# አጭር ዜና-መዋዕል



እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የ21ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ስኬታማና ስመጥር አፍሪካዊ የሥነጥበብ ባለሙያ ናቸው። አፈወርቅ በ1925 ዓ.ም በአንኮበር ከተማ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወለደ። በልጅነቱ በቤቱና በከተማው ዙሪያ እንዲሁም በመደበኛ የትምህርት ክፍለ-ጊዜዎች ሥዕል ይስል ነበር፤ በኋላ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድጋፍ ከሌሎች በርካታ ታዳጊዎች ጋር በ15 ዓመቱ ወደ እንግሊዝ አገር የማዕድን ኢንጅነሪንግ ትምህርት እንዲያጠና ተላከ። ሆኖም የሥዕል ፍላጎቱና ዝንባሌው ስላደላ በለንደን የኪነጥበብ ማዕከላዊ ትምሕርት ቤት (Central School of Arts & Crafts) ገብቶ ትምሕርቱን ተከታትሏል፤ በመቀጠል ለከፍተኛ ጥናት በለንደን ዩኒቨርሲቲ ስሌድ የሥነጥበብ ማዕከል (Faculty of Fine Arts at Slade) በመግባት ስዕል፣ ቅርፃ-ቅርፅ እና ሥነ-ሕንፃን በማጥናት ለት/ቤቱ የመጀመሪያ አፍሪካዊ ተማሪ ሆኖ አጠናቋል።

በ1946 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ለሃገሩ የመጀመሪያ የሆነውንና የግሉን ዐውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ካሳየ በኋላ ለ2 ዓመታት በአውሮፓ ከተሞች ለመጓዝ እና ለመማር የሚያስችል ገንዘብ በማግኘቱ ወደ አውሮፓ በመመለስ የተለያዩ የሥነጥበብ ሥራዎች ያሉባቸውን ከተሞች የመጎብኘትና ተጓዳኝ ትምህርቶችን የመከታተል እድል አግኝቷል። በ1956 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የክብር ሽልማት የተቀበለ የመጀመሪያው (የሥነጥበብ ባለሙያ) ሲሆን ዝናው በዓለም-አቀፍ ደረጃ ሲናኝ ሥራዎቹን ለማሳየት፣ ንግግር ለማድረግ እና በርካታ የክብር ሽልማቶችን ለመቀበል ወደ ብዙ ሀገራት ተጋብዞ ሄዷል።

አፈወርቅ በህይወት ዘመኑ የላቁ ሥራዎችን በመሥራት ሀገሩን ለዓለም ያስተዋወቀ ሲሆን በዓለማችን በሥራቸው ከተመረጡ 200 ሰዎች አንዱ በመሆን የህይወት ታሪኩና የሀገሩ ሰንደቅ-ዓላማ ወደ ጨረቃ ተወስዶ ተቀብሯል። ታዋቂ ከሆኑት ሥራዎቹ መካከል “የመስቀል አበባ”፣ “እናት ኢትዮጵያ” እና የአፍሪካውያንን ያለፈ ሀዘን፣ የአሁን ትግል እና የወደፊቱን ተስፋ የሚወክለው ባለቀለም የመስታወት ሥዕል (stained glass art) ከታዋቂዎቹ መካከል ናቸው። ይህ ታላቅ የሥነጥበብ ባለሙያ በ2004 ዓ.ም በሰማንያ ዓመታቸው በድንገተኛ ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የአፈወርቅ ሥራዎች በኢትዮጵያ እና በዓለም ዙርያ የሚገኙ ሲሆን ሀገርቤት የሚገኙትን ሥራዎቹን እና ራሱ ቀይሶ ያሠራውን “ቪላ አልፋ” መኖሪያ ቤቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በኑዛዜ አበርክቷል።

Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 5 4/14/2022 12:18:15 PM



Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 6 4/14/2022 12:18:18 PM



# አፈወርቅ ወልደ ነጎድጓድ

## አያልነህ ሙላቱ (ደራሲ)

ኪነ-ጥበብ ዘለዓለማዊት ስትሆን፣ ጊዜ ግን ሯጭ ናት። በሳል የኪነ-ጥበብ ሥራዎች የተፈጠሩት ራሳቸውን እና ጊዜያቸውን ለዚሁ ሙያ አሳልፈው በሰጡ፣ ጥልቅ ምጥቀት ባላቸው ጨዋ ታላላቅ ጠቢባን ጥረትና ብርታት ነው። ያስኳላው ዕውቀት የጥበብ ቆሌውን አዳባሪ እንጂ የጥበብ መሠረት አይደለም። ትምህርት እና የተፈጥሮ ችሎታ ሲጋቡ በሳልና ደረጃዋን የጠበቀች ጥበብ ትወለዳለች። ለአንድ አርቲስት እራሱ አምጦ ከወለዳትና ጥበባዊ እስትንፋስ ከዘራባት ፈጠራው ውጪ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው። የወለዳቸው ልጆቹ እንኳ ቢሆኑ፣ የስሙ መጠሪያ እንጂ የስሙ መከበሪያ አይሆኑም። ከተባረኩ ጥቂቶች በቀር ሁሉም ልጆቹ የአርቲስቱን ስም በሸጋ ያስጠራሉ ብሎ ማመን ይቸግራል።

የኪነ ጥበብ ሀብቷ የፈጠራ ውጤቷ ነው፤ የፈጠራ ሀብቷ መገኛ ደግሞ ፈጣሪዋ ነው። ታታሪ የፈጠራ ሰው ያገባች ጥበብ በስሟ የተከበረች በሀብቷ የበለጸገች ናት። ባንጻሩም ተልካሻ ባል ያላት ጥበብ የተናቀ ስምና የምትበላው ያጣች ምስኪን - ድሃ ትሆናለች። የጥበብ ሰው ቆዳውን ገልብጦ የለበሰ የሕዝብ ልጅ ነው። በሕዝብ ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት በደል ወይም የከፋ-ጥቃት ይሰማዋል። ጠቢቡ በሕዝብና በመንግሥት መካከል ፍትሃዊ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ይጠበቅበታል። የሒስ ሰይፉም ሳያዳላ ቀጥ ብሎ የቆመና በአጥፊው ላይ ሚዛናዊ ፍርድን የሚሰጥ ዳኛ ነው። መንግሥትን በጥፋቱ የሚገስጥ ደፋርም ነው። ሕዝብንም ከስህተቱ የሚያርም አስተማሪ ነው። የዛሬን አያድርገውና፤ በድሮ ጊዜማ እረኛ፣ አዝማሪ፣ አስለቃሽ፣ ሠዓሊ፣ ደብተራ. . . ምን አለ? ሳይል ዘውድ የሚጭን፣ መንገድ የሚጀምር፣ ጦርነት የሚገጥም መሪ አልነበረም።

ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ የአርቲስት ህይወት ተምሳሌት ነው። "አርቲስት ለማኝም ተመጽዋችም አይደለም፤ ክብሩም ዝቅ ያለ መሆን የለበትም" ባይ ነው። በዘር ወይም በደም ሳይሆን እራሱን በሥራው ልዑል ያደረገና እራሱ መሬት ገዝቶ በገነባው ቤተ-መንግሥት መሰል ግቢ ውስጥ የሚኖር ኩሩ የጥበብ ሰው ነበር። በዘመኑ የነበሩ አንድ ባለሥልጣን "ለምን ሰማይ ሰማይ ታያለህ አንገትህን ለምን ዝቅ አታደርግም?" ቢሉት፣ "ጌታዬ! የመሬቱንማ አይቼዋለሁ... ማየት የምፈልገው የሰማዩን ነው!" ብሏቸዋል።

ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ሥራውንና ስሙን የሚያስጠብቅ ንቁና ጥንቁቅ የፈጠራ ሰው ነበር። አርቲስቱ በዓለም ዙሪያ የተሰጠው ረዘም ያለ የማዕረግ መጠሪያ ስም አለው። ከተንኮል ወይም ከንቀት አሊያም ከቅናት በመነጨ የማዕረግ ስሙን በትክክል ሳይጠቅስ የግብዣ ወረቀት ለላከ ጋባዥ መልስ አይሰጥም፤ በጥሪው ቦታም ላይ አይገኝም። ለዚህም በቂና አጥጋቢ መልስ አለው። "ማዕረጉን አክብረው የሰጡኝ ሰዎች አክብሬ እንዳስከብረው ነው። ማስከበር ካልቻልሁ ደግሞ መጀመሪያውኑ መቀበል አልነበረብኝም" ይል ነበር።

ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በፈጠራው ሙሉ ለሙሉ የሚተማመን፣ ኑሮውንም በሙያው በሚያገኘው ገቢ ላይ የገነባ ጠቢብ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ከትምህርት ቤት ሲመለስ በአንድ እጁ ስልጣን በሌላ እጁ ጥበብን ይዞ ሕይወቱን እንዲመራ ፈልገው ለሹመት አጭተውት ነበር። እርሱ ግን "የመንግስት ተቀጣሪ መሆን አልፈልግም... እግዚአብሔር ያሳይዎ! ክርስቶስ ያመልክትዎ! የተማርሁት በሙያዬ እራሴን ለመገንባት ነው" ብሎ እግራቸው ሥር ወድቆ ለምኖ ሹመቱ ተነስቶለታል።

አርቲስቱ በአቋሙ ጸንቶ ቃሉን ጠብቆ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ ጥበብን ሲያገለግል ኖሯል። ሥራዎቹም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በመላው ዓለም ታዋቂ ሆነው የራሳቸውን የክብር ቦታ ይዘዋል። በእነዚህ የጥበብ ሥራዎቹ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ መላው ዓለም ይማርባቸዋል፤ ያውቅባቸዋል፤ ይመራመርባቸዋል። የአፈወርቅ ፈጠራዎቹ ብቻ ሳይሆኑ፣ የአኗኗ ዘይቤው፣ የህይወት ፍልስፍናው፣ የተለዩ የእናት አገር ፍቅሩ፣ ሃይማኖታዊ ብቃቱ፣ የረጅም ጊዜ የብህትውና ሕይወቱ፣ ገና ወደፊት በዝርዝር መጠናት ያለበት ነው።



፯

# በቀለ መኮንን (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

## ሠዓሊ፣ ቀራጺና መምህር - በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የሥነጥበብ የሥራ ቡድን ሲቀ-መንበር

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ትልቁን የሥነጥበብና ያደባባይ ሰው አፈወርቅ ተክሌን በዚህ ብዛትና ዓይነት ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ ላደባባይ ማቅረቡ ትልቅ ትርጉም ያለው ተግባር ነው። የትርዒቱ ስብስብ እጅግ የተከበሩ ሜትር አርቲስት የዓለም ሎሪየት አፈወርቅ ተክሌ በተለያዩ ዘዬዎች ካደረጓቸው ሙከራዎቻቸው አንጻር ከሞላ ጎደል የሥነሥዕል ሕይወታቸውን ጉዞ በምልዐት የሚያስቃኝ ነው። እኒህ ትልቅ የሥነ ጥበብ ሰው ከመደበኛው የሥነጥበብ ክንዋኔያቸውና ጥለውልን ካለፉት ውድ ኪነጥበባት ባለፈ በአስደናቂ ማንነታቸው ዙሪያ ስለሕይወት ስለሀገር ስለሙያ ስለጊዜ ስለተዝናኖት ስለእምነት እና ስለ ሌሎችም ዝርዝር አመለካከቶቻቸው ትውልዶች ሊማሩባቸው የሚችሉ አያሌ ዕሴቶችን ጥለው ያለፉ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ናቸው።

# ጌታ መኮንን

## ሠዓሊ

እኛ ባደግንበት የልጅነት ዘመን ከሠዓሊ አንድ፣ ከዘፋኝ አንድ፣ ከደራሲ አንድ፣ ከገጣሚ አንድ፣ ከሩዋጭ አንድ ተመርጦ ብቸኛው እየተባለ የሚጠራበት Monolithic culture የሰፈነበት ዘመን ስለነበር፣ በየመንደሩ ሥዕል የምንሞጫጭር ሁሉ ያው አንድየውን አፈወርቅን ትተካለህ እየተባልን ነው ያደግነው፤ ውለን አድረን ነው ማንንም መተካት እንደሌለብንና ራስን መሆን እንደሚሻል የገባን። በ19 ዓመቴ የመጀመሪያ ኤግዚቢሽኔ ላይ የክብር እንግዳ ሆኖ ተጠርቶ ነበር አፈወርቅን የተዋወቅሁት፣ ከዚያም ስልክ ቁጥሩን ሰጥቶኝ እየደወልኩለት ብዙ እንገናኝ ነበር። ከዚያም አጋጣሚ ሆኖ ወደ እንግሊዝ አገር የትምህርት ዕድል አግኝቼ እሱ የተማረበት የሥዕል ትምህርት ቤት Slade School of Art ስሔድ፣ በደርግ ዘመን በመገናኛ አካባቢ ይኖርባት በነበረችው አነስ ያለች ቤቱ ከተወሰኑ ወዳጆቼ ጋር ግብዣ ጠርቶን አሸኛኘት አድርጎልኛል። ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን ካካፈለኝ በኋላ ተምሬ ወደሃገሬ እንድመለስና አገሬ ላይ እንድሠራ አጥብቆ መክሮኝ ተለያየን። እኔም በተሠጠኝ ምክር መሠረት ከስድስት ዓመት በኋላ ትምሕርቴን ስጨርስ ጓዜን ጠቅልዬ ወደ ሀገሬ መጣሁ። እንደመጣሁም ደውዬ ቀጠሮ ከያዝኩ በኋላ በቀጠሮዬ ተገኝቼ መመለሴን ነግሬው ብዙ ጠቀሚ ምክሮች ተለገሶኝ ተለያየን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አልፎ አልፎ እየተገናኘን ብዙ ጭውውቶችን እናደርግ ነበር። እቤቱ ሄዶ የሚያውቅ ሰው ሁሉ ሊመሰክር እንደሚችለው፣ በቤቱ የሄደን እንግዳ የመጣብኝ ብሎ ሳይሆን የመጣልኝ ብሎ በሚደንቅ ሁኔታ ሽርጉድ ብሎ ነበር የሚያስተናግደው። ወደሱ ዘንድ ለመሄድ ስደውል አንድ ሰዓት ነው ያለኝ ብሎ ይፈቅድልኝና በኋላ ስሄድ ግን ብዙ ሰዓቶች ወስዶ ጠለቅ ያለ ጭውውት እናደርጋለን።

እኔ ጋሽ አፈወርቅ ነበር የምለው። በመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ብጠራው ቅር ይለው እንደሁ ስጠይቀው፣ ካለምንም ማንገራገር ከፈቀደልኝ በኋላ፣ ለምን ሙሉ የክብር ስሙ እንዲጠራ እንደሚያስገድድ በጣም ረዘም ያለ ማብራሪያ ሰጠኝ። ይሄ ሁሉ መጠሪያ ማዕረጎች በብዙ ፈተና የተገኙና ለማንም አፍሪካዊ ያልተሰጡ የሙያ ክብሮች መሆናቸውንና ከአዞ መንጋጋ ፈልቅቆ ያወጣቸው መሆኑን ይነግረኝ ነበር። ሰዎች ሆነ ብለው ስሙን ከነሙሉ ማዕረጉ መጥራት ያለመፈለጋቸውን ሲያውቅ ምላሹ በተለያዩ መድረኮች እንደሚታወቀው ቆጣ ያለ ነበር። ይህም ለሚወክለው ሙያ ካለው ከፍተኛ ክብርና ሃላፊነት የመነጨ እንጂ ለግል ክብሩ ብቻ ተጨንቆ እንዳልነበረ ተረድቻለሁ። ባደገበት ዘመን ከሱ ቀድሞ ሙያውን ያስከበረ ግዙፍ ስም ባለመኖሩ፣ የዘመኑ ባለስልጣናት እጀ-ሠሪ ብለው ዝቅ ሊያደርጉት ቢሞክሩም ሁሉንም አሸንፎ ከፍ ብሎ የታየ የጥበብ ኮከብ ነው።

እኔ የደረስኩበት ሰውዬ በሩቁ ስለሱ ከምንሰማው ሁሉ የገዘፈና ላቅ ያለ ሰብዕና ያለው (larger than life) ሊባል የሚችል አስተዋይ፣ አንደበተ-ርቱዕ፣ ብልህ፣ ደግ፣ ሀገር ወዳድ፣ መካሪ አባት፣ ብዙ ብቃትና ክህሎት ያለው ርቆ የሄደ ሠዓሊ ነበር። በርግጥም ግዙፍ ሰው ነበር። አፈወርቅ ስለጥበብ፣ ስለባህልም ሆነ ሌሎች ዓለማዊ ጉዳዮች ላይ ያለው ግንዛቤና እውቀት ጥልቅና ረቂቅ ስለነበረ ተሰምቶ አይጠገብም። በተለያዩ የሥዕል ሙያ ዘርፎች ሁለገብ ብቃት ያለው ጠቢብ ሲሆን ማንኛውንም የሥዕል ቁስ አንስቶ በሚያስደምም ብቃት ይራቀቅበታል፣ ይህም በእንግሊዝኛው አገላለጽ 'Renaissance man' ሊያስብለው ይችላል።

በኔ ዘመን፣ አፈወርቅ በሠዓሊ ሕይወታችን ሁለት ጊዜ ብቅ ይላል። በመጀመሪያ ገና ጨቅላ ሳለን ጀምሮ ሠዓሊ ለመሆንም ሆነ ለመባል በጉጉት ስንንጠራራ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ትምህርታችንን ጨርሰን ወደ ገሃዱ ዓለም ስንወጣ፤ እሱ በከፈተልን ጭላንጭል ቀዳዳ ጥበብን ፍለጋ ስንዋትትና በሙያችን ተቀባይነት ለማግኘት ስንፋለም ከፊታችን ከፍ ብሎ ይታየናል። አንዳችንም ድጋሚ ልናደርገው በማያስፈልገን ሁኔታ በማንኛውም መድረክ ሙያውን ለማስከበር በከፈለው መጠን ባለውለታችን ነው።

# አገኘሁ አዳነ ድልነሣሁ

## ሠዓሊ፣ መምህርና የአለ የሥነጥበብና ዲዛይን ት/ቤት ዳይሬክተር


አፈወርቅ ተክሌ በኢትዮጵያ የሥነ ጥበብ ልምምድ ከፍተኛው ቦታ ላይ የተቀመጠ፤ በስምና ዝና የናኘ/የተናኘ፣ ቆመን ብንንጠራራ የማንደርስበት ገናና ማንነት ነበረው። በተለይ ለኛ ለወጣንያን mythic figure ነበር ማለት ይቻላል። በመጀመርያ ከዚህ ገናና ሰዉ ጋር የሚነገርለትን በማድመጥ ተዋወኩት። በመቀጠል፣ በህትመት ተራብተው በየቤቶቻችን በገቡ ሥዕሎቹ (Reproductions) ስለ አፈወርቅ የበለጠ ለመረዳት ቻልኩ። በሰማንያዎቹ መጀመሪያ አካባቢ እማርበት በነበረ ት/ቤት ቤተ መፅሃፍት ዉስጥ ሪቻርድ ፓንክረስት (Rechard Pankhurst) የጻፈውን የአፈወርቅ ተክሌ የሥዕል ሥራና የሕይወት ታሪክ የያዘ መጽሐፍ በማግኘቴ የበለጠ ስለ ሠዓሊው ለማወቅና ለመመርመር እድል አገኘሁ። እንደ ጀማሪ ሠዓሊ ብዙዎቹን የአፈወርቅን ሥራዎች መገልበጥና ማጥናት ቻልኩ። የሥዕል ግንዛቤ መሠረቱ የማያቋርጥ ልምምድና አስተውሎት በመሆኑ፣ ከመጽሐፉ ጋር የጠበቀ ዝምድና መሠረትኩ። ብዙ ተማርኩበት። ጥረቴም በጓደኞቼና በመምህሮቼ ዘንድ ከፍ ያለ ተቀባይነት እንዳስገኘልኝ አስታውሳለሁ። ከሥዕል ውጭ ባሉ ትምህርቶች ጥሩ ውጤት የነበረኝ ቢሆንም የሥዕል ፍቅሬ የበረታ መሆኑን የቀዳኋቸው የአፈወርቅ ተክሌ ሥዕሎች ምስክር ሆኑኝ። ለሥዕል ትምህርት እጅ ሰጠሁ።

1986 ዓ.ም አዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ት/ቤት በአሁኑ ስሙ አለ የሥነጥበብና ዲዛይን ት/ቤት ገባሁ። ትምህርቴን እከታተል የነበረው ከመገናኛ እየተመላለስኩ ነበር። መኖርያዬ ከአፈወርቅ ተክሌ ቤት ዝቅ ብሎ ስለሆነ ዘወትር እሁድ ጠዋት ጠዋት በአካል ዓየው ጀመረ። አራት ዓመት ያህል እዚያ ሰፈር ስኖር ስለአፈወርቅ የሚነገሩትና የሰውየው የመንፈስና የአካል ግዝፈት አስፈርቶኝ እንደሁ አላውቅም ከማየት ውጭ ለማናገር አልደፈርኩም። ከት/ቤት ከወጣሁ ከዓመታት በኋላ በዕለተ እሁድ፣ በየካ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጎንለጎን ቆመን ቅዳሴ ተካፈልን። ያ ቀን ስለ አፈወርቅ የተለየ ነገር ያውኩበት ዕለት ነበር። ቅዳሴው አልቆ ታቦተ ህጉ ዑደት ሲያደርግ አሁንም ተገናኘን። በማላውቀው ምክንያት ስሜን ጠየቀኝ። ነገርኩት። የትልቅ ሰው ስም እንደያዝኩ ነገረኝ (አገኘሁ እንግዳ/ን ማለቱ ነው)።

ሲነገር እንደምሰማው አፈወርቅ የማዕረግ ስሙን ለገደፈ ሰዉ ምንም ይቅርታ እንደሌለው ነበር። እኔ ደግሞ በጊዜው አሟልቼ ለመጥራት እቸገር ነበር። ሳሟላ ቅደም ተከተል እስታለሁ፤ ቅደም ተከተል ልጠብቅ ስጥር አንዱን ወይ ሁለቱን ማዕረግ እገድፋለሁ። በዚህ ምክንያት ያን ቀን ንግግር ለመጀመር እጅግ ተቸገርኩ። በስተመጨረሻ ጨክኜ "የኔታ የመሥርያ ቦታህን እንዳይ ፍቀድልኝ" ብዬ ጠየኩት። ገጹ ላይ የሚገርም ብርሃን ዓየሁ፤ በደስታና በፈገግታ የሚቀጥለው ሳምንት እሁድ ቀጠሮ ሰጠኝ። በማውቀው የአክብሮት አጠራር በመጠቀሜ ትልቅ ቡራኬ እንዳገኘሁ አስታውሳለሁ።

ታላቁ ጠቢብ "እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ" ሰው በሚያውቀው ልክ፣ በዕውነት ያለሐሰት ቢቀርበው የሚቀበል ትሁት ሰው መሆኑን ተማርኩ።

Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 9 4/14/2022 12:18:23 PM




፯



፰



፱


፲


፲፩

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | የአፍሪካ ገጽታ (የፊት ሽፋን) \| African Atmosphere (Front Cover) | የዘይት ቀለም ቅብ በሸራ ላይ | 125 X 100 ሳ.ሜ | 1967ዓ.ም |
| ፪ | የአፍሪካ የቅርስ ጥናት \| Study for African Heritage | የዘይት ቀለም ቅብ በሸራ ላይ | 76 X 50 ሳ.ሜ | 1972ዓ.ም |
| ፫ | ስቅለት \| Crucifixion | የዘይት ቀለም ቅብ በእንጨት ቦርድ ላይ | 102 X 76 ሳ.ሜ | 1953ዓ.ም |
| ፬ | ርዕስ አልባ \| Untitled | የዘይት ቀለም ቅብ በሸራ ላይ | 125 X 100 ሳ.ሜ | 1953ዓ.ም |
| ፭ | የቤት እመቤት \| The house wife | የዘይት ቀለም ቅብ በእንጨት ቦርድ ላይ | 100 X 65 ሳ.ሜ | 1953ዓ.ም |
| ፮ | ሽንኩርት የቁስ ጥናት \| The onion still life | የዘይት ቀለም ቅብ በወረቀት ላይ | 44 X 34 ሳሜ | 1950ዓ.ም |
| ፯ | ኢትዮጵያዊያኖች የጀት ኤንጅን ሲሠሩ \| Ethiopians Working on Jet Engines | ኢንክ ቀለም በወረቀት ላይ | 30 X 45 ሳ.ሜ | 1963ዓ.ም |
| ፰ | የመልክ ጥናት \| Portrait study | ኢንክ ቀለም በወረቀት ላይ | 32 X 25 ሳ.ሜ | 1953ዓ.ም |
| ፱ | የካምፐሪጅ ፕሮፌሰር \| Cambridge Professor | የዘይት ቀለም ቅብ በእንጨት ቦርድ ላይ | 44 X 33 ሳ.ሜ | 1952ዓ.ም |
| ፲ | በቢሾፍቱ ሃይቅ በኩል \| By Bishoftu Lake | የዘይት ቀለም ቅብ በሸራ ላይ | 84 X 43 ሳ.ሜ | 1975ዓ.ም |
| ፲፩ | የመልክ ጥናት በቀበሌ ስብሰባ ወቅት \| Study faces from Kebele Meeting | ኢንክ ቀለም በወረቀት ላይ | 58 X 48 ሳ.ሜ | 1961ዓ.ም |





የአፈወርቅ አብዛኞቹ ሥራዎች የሚገኙበትና ራሱ ፕላን አውጥቶ ያሠራው “ቪላ አልፋ” ስዱዲዮ/መኖሪያ ቤት የውጭ ገጽታ።

በእንግሊዝና አውሮፓ በቆየባቸው ጊዜያት ይጠቀምባቸው የነበሩ የውሃ ቀለም መሥሪያ ቁሳቁሶች።

አዘጋጅ፤ ይታገሱ ጌትነት
ረዳት አዘጋጆች፤ ግርማ ቡልቲ፣ ሙሉአዳም አዳነ፣ ይድነቃቸው ሙሉጌታ
ዲዛይንና ፎቶግራፍ፤ ቴዎድሮስ ክፍሌ
ጽሑፍ ኤዲቲንግ፤ ቴዎድሮስ አጥላው
ህትመት፤ ተዋነይ ስቱዲዮ

ምስጋና
ለአዲስ አበባ ብሔራዊ ሙዚየም፤ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን
ለየኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ
ለአለ የሥነጥበብና ዲዛይን ት/ቤት
ለሮሚና ሬስቶራንት

Afework Tekles Catalog APR14-2022.indd 12 4/14/2022 12:18:39 PM